# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

## የአሸባሪዎችን አገዛዝ ለመግታት በጋራ እንነሳ!

ከአለፈው የቀጠለ.....

**ክፍል ሁለት፤**

ዛሬ በዚህ መልክ ከምንገኝበት ወሳኝ የፈተና ወቅት በድል አድራጊነት ለመውጣት ሕዝባችን ከራሱ ተጋድሎ ሌላ ምንም ይሁን ምን መድኅን እንደሌለና እንደማይኖር ተገንዝቦ በራሱ፥ በቆራጥነቱና በአንድነቱ ብቻ ተማምኖ ከእንግዲህ ለዴሞክራሲ መስፈን ብቻ ሳይሆን አገሩ እንደ አገር፥ ሕዝቡ እራሱ እንደ ሰብዓዊ ፍጡር ኅልውናቸው ጥያቄ ውስጥ ገብቷልና የተያዘውን የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትንንቁን ከመቀጠልና ድሉን ከማስከበር ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም፡፡ ታጋይ ድርጅቶቹም ይኸንን እውን ከማድረግ ሌላ ተቀዳሚ ተግባር ሊኖራቸው አይችልም፡፡

ለዚህ ደግሞ ዛሬ ከፊታችን ከተደቀኑት ችግሮች ባሻገር እጅግ በጣም አመች የሆነ ሁኔታ ውስጥ ነን፡፡ በተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና በኅብረተሰባችን ውስጥ ባሉት ሌሎች ግንባር ቀደም ዴሞክራቶች ዘንድ ጥናቱና ጥራቱ፥ ሕዝባችን የሚያሳየው አኩሪ ቆራጥነት በቀጣይነት እስካለ ድረስ በግንቦት ሳቢያና እየተከፈለ ባለው መጠነ-ሰፊና ፈርጀ-ብዙ ከባድ መስዋዕትነት የተፈጠረው አጠቃላይ ሁኔታ ያለ አንዳች ጥርጥር ለዴሞክራቶች የሚያደላና የኢትዮጵያን የመከራ ዘመን ማክተምና ትንሳኤዋን የሚያበስር መሰረታዊና ተጨባጭ የኃይል ሚዛን አለ፡፡

በአንድ በኩል ከሰባ ሰባት ሚሊዮን ሕዝባችን የማያወላዳ አብላጫው ክፍል ይኸ ምርጫ ተጭበርብብሯል፥ ድምፄ ተሰርቋል፥ ድሌ ይከበርልኝ እያለ በሰላማዊና ሕጋዊ ትግል እየተሰዋም ቢሆን ለመግፋት የቆረጠበት ሕዝባዊ ማዕበል አለ፡፡ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ታጋይ ዜጎች ደግሞ ይኸንን የሕዝብ ድምፅ ሰምተው ይኸንን የሕዝብ ህልም እውን ለማድረግ በያለበት በሕዝቡ ውስጥ ተተክለው በጀግንነትእየተዋደቁና እየተሰው እንዲሁም ለቀጣይ ትግል ዝግጁ መሆናቸውን እያሳዩ ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በውጭው ዓለም የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ይኸንን ሕዝባዊ ተጋድሎ በሃሳብ፥ በጉልበት፥ በገንዘብና በዲፕሎማሲ ትግል ለማገዝ ቆርጠው ተነስተው በያለበት የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በሕዝብ ድምፅ ተሸንፎ፥ ሕዝባችን ለለውጥ ያለው ቁርጠኛነት ከተራ አፋኝ አገዛዝነት አልፎ በመንግሥት ደረጃ ሽብር ከመንዛት ሌላ ምንም አማራጭ የሌለ መስሎት ኅብረተሰባችንን በዳግም ቀይ ሽብር ማንበርከክ እችላለሁ ብሎ የተነሳ የጥቂቶች ፀረ-ሕዝብ ቡድን ኢሕአዴግ አለ፡፡

ዛሬ ለአገራችን በጎ ነገር፥ ለዚህ ሕዝባችን የተሻለ ቀን አመጣለሁ ብሎ የሚነሳ ማንም ኃይል የፖለቲካ ድርጅት ሆነ የሲቪክ ስብስብ፥ የውጭ ሆነ የውስጥ ኃይል፥ ማንም ዴሞክራት ሆነ አገር-ወዳድ ዜጋ ስለተያዘው ትግል ሃሳብ ሲሰነዝርም ሆነ ስልት ሲቀይስ ከዚህ የኃይል ሚዛንና ከመሠረታዊው የድምፄ ይከበር የሕዝብ ጥያቄ ተነስቶ የትግሉ ዋና ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚሊዮን እያስቆጠረ የማንቀሳቀስ ዓላማ ይዞ በመነሳት ይኸንን ሕዝባዊ ማዕበል መንከባከብ ይኖርበታል፡፡

*ከዚህ የኃይል ሚዛንና በሱ ብቻ ተማምኖ የትግል ስልት መቀየስ ከተባለ ደግሞ አጀንዳችንም ሆነ ስልታችን በማያወላዳ ሁኔታ ግልፅ ይሆናል። በአጭሩ እናስቀምጠው ካልን ደግሞ በአንዲት ወቅታዊ መፈክር የሚጠቃለል ይሆናል። ይኸውም "ለሕዝባዊ አጀንዳ በሕዝባዊ ትግል" የሚል መፈክር ነው።*

*ለመሆኑ ሕዝባዊ አጀንዳ ስንል ምን ማለታችን ነው?*

*ሕዝባችን ባለፉት ወራት ልጆቹን የሰዋውና የሚጠበቅበትን ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጦ የተነሳው የተነጠቁ የግንቦት ድሎቹን መልሶ እጁ ውስጥ ለማስገባት ነው። የእኛም የትግል አጀንዳ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ በዚህ ሕዝባዊ አጀንዳ ዙሪያ መቃኘት ይኖርበታል። ይኸንን ሕዝባዊ ዓላማ ከግብ የምናደርሰው ደግሞ ወይ በአጠቃላይ የግንቦቱ ምርጫ ሂደት በአዲስ መልክ በተዋቀረና ሁሉም ወገኖች በተስማሙበት ገለልተኛ አካል ተገምግሞ ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊ እልባት ሲያገኝ ወይ ደግሞ ሌላው ቀርቶ ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብም ለመጭበርበሩ የምስክር ቃል የሰጠበት ምርጫ በሌላና ሁሉም በተስማማበት የምርጫ ቦርድ ፥ በሌላና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ሲደገም ብቻ ነው።*

*በመሆኑም ላለፉት ስድስት ወራት የኢሕአዴግን መሪዎች የሕዝብ ድምፅ አክብሩ እያልን ስንጮህ እኛ የሕዝብ ድምፅ አለማጻመጣችን ፈጽሞ የማይታሰብ ጉዳይ ስለሆነ፥ ላለፉት ስድስት ወራት የፈሰሰውን የልጆቻችን ደምና የወላጅ እንባ እንደ ቀጭን ውሃ ቆጥራችሁ አታዋርዱት እያልን ከኢሕአዴግ መሪዎች ጋር እየተሟገትን እኛ "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" እያሉ የወደቁትን ዜጎች ሰማዕትነት አለማክበራችን ጭራሽ የማይታለም ጉዳይ በመሆኑ፥ የኢሕአዴግ መሪዎች በውጭም ሆነ በውስጥ የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎች የሚያካሂዱትን ተጋድሎ ሚዛን የማይደፋና የትም የማያደርስ የጥቂቶች መፍጨርጨር አድርገው ሲንቁት እኛ ለዚህ ሕዝባዊ ማዕበል ጆሮ ዳባ ልበስ የምንልበት የታጋዮች ንቀት ባህል ስለሌለን ከዚህ የሕዝብ ድምፅ ከማስከበር በመለስ የምንረካበት ምንም ዓይነት ድል እንደማይኖር ለሚመለከተው ሁሉ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ይኖርበታል።*

*ሕዝባዊ ትግል የሚለው መፈክራችንም ግልፅ ነው። የእኛ ሚና ትግሉን ማስተባበርና በየወቅቱ ከሚከሰቱት አዳዲስ ሁኔታዎች እየተነሳን ለትግሉ አቅጣጫ መስጠት ስለሆነ በምንም መልክ የሕዝቡን ትግል እተካለሁ ብሎ የሚኳትን አደገኛ ስልት አይኖረንም። ዓላማችን የኢሕአዴግ መሪዎች የሕዝቡ ድምፅ ስለሚከበርበት ሁኔታ ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጡና ለእኛም፥ ለእነሱም ለሕዝባችንም የሚበጅ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መፍትኄ ላይ ለመድረስ ነው። ከዚህ በመለስ የምንደራደርበት ምንም ዓይነት ፍርፋሪ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም አደገኛ የኢሕአዴግ መሪዎች በሕዝብና በዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ግፊት የድርድርን አሳብ ከተቀበሉ የድርድሩ አጀንዳ የሕዝብ ድምፅ ይከበር በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ተረቅቆ በቅድሚያ ለሕዝብና ለአገሪቱ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በሙሉ በግልፅና በይፋ መቀመጥ ይኖርበታል። ሁለተኛ ይኸ የድርድር ጥሪ ተቀባይነት ቢያገኝም በዚህ ተሞኝተን ሲያመቻቸው በኃይል አመፃቸው፥ ሳያመቻቸው በመለሳለስ የሕዝቡን ትግል ከማደናገርና ከማሰናከል ለማይመለሱት የኢሕአዴግ መሪዎች የሕዝባዊ ትግሉን ቅስም ለመስበር እንዳይጠቀሙበት ከእንግዲህ ማንኛውም ከነሱ ጋር የሚደረግ ድርድር ኅብረተሰባችን ከዳር እስከዳር በሚያደርገው እንቅስቃሴ የታጀበ ብቻ መሆን እንደሚኖርበት በድጋሚ መግለፅ እንወዳለን።*

*የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ከነዚህ ነጥቦች በመነሳትና ለነዚህ ዓላማዎች መሳካት የሕዝባችን እንደ አንድ ሰው ሆኖ የሚያደርገው የተባበረ የእንቅስቃሴ ማዕበል ቀጣይነት ወሳኝ መሆኑን በማመን፤*

አንደኛ፡- የሰኔው የንፁኃን ደም ሳይደርቅ ጥቅምት ላይ በተደገመው ግፍ የግንቦት ተጋድሎ ምዕራፍ የተዘጋ ለሚመስላቸው ለውስጥም ሆነ ለውጭ ኃይሎች ሁሉ ትግሉ ይቀጥላል የሚል ግልፅ ሕዝባዊ መልዕክት ለማስተላለፍ፤

ሁለተኛ፡- በወያኔ/ኢሕአዴግ የጉልበት አመፅ ተበግሮ ሕዝባችን የትጥቅ ትግሉን እንዳልፈታና ኅብረተሰባችን ለፀረ-ሕዝቦች ተንበርክኮ ለሌላ ገደብ ለሚስትና መጠን ላጣ የአፈና፥ የግድያና የግፍ ውርጅብኝ እራሱን ላለማመቻቸት ሲል ተጋድሎውን ለመቀጠል አስፈላጊ የሆነው ወኔውም ይሁን ቁርጠኛነቱ እንዳለው ለማብሰር፤

ሦስተኛ፡- ዘላቂው የሕዝብ ድምፅን  የማስከበር ዓላማ እንዳለ ሆኖ የሰኔው ደምና እንባ ሳይደርቅ የአቶ መለስ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደገና ባወጀው የሽብር ጦርነት በሚደርስበት ግፍ እንደተቆጣና ለፈሰሰውና እየፈሰሰ ላለው ደም ተጠያቀዎቹ ለፍርድ ቀርበው ተገቢ ቅጣታቸውን እንዲያገኙ፥ ከየቤታቸው ታፍሰው ለዱር አራዊትና ለተለያዩ በሽታዎች ተጋልጠው የሚገኙ ልጆቻችንን ባወጣ ያውጣቸው ብለን እንዳልተውናቸውና በአስቸኳይና ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ ተፈትተው ከቤተሰቦቻቸው እንዲደባለቁ ለመታገል ያለንን ውሳኔና ቁርጠኝነት ለማሳየት፤

አራተኛ፡- በሰላማዊና ሕጋዊ ስልት ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅድላቸው መሠረት ተሰማርተው መታገላቸው ከወንጀል ተቆጥሮባቸው ለእስር የተዳረጉት የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ መሪዎችና ደጋፊዎች፥ የነፃው ፕሬስ አባላት፥ የሲቪል ማኅበረሰቡ ድርጅቶች መሪዎችና ሌሎች ታጋዮች ሁሉ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ለመጠየቅ፤

ለመስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም በቅንጅቱና በኅብረቱ ተጠርቶ የነበረው የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ታቅዶ በነበረባቸው ከተሞች በሙሉና በሌሎችም ጭምር እንደገና እንዲቀሰቀስ፥ ይኸም በውጭው ዓለም በአራት ክፍለ ዓለማት በትላላቅ ከተሞች ላይ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎቻችን ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ታጋይ ወገናቸው አጋርነታቸውን እንዲገልጹ ለማስቻል በአንድ በኩል ለሕዝባችንና ለኅብረተሰቡ ግራ መጋባትና ለትግሉ መዳከም፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለፀረ-ሕዝብ ኃይሎች እብሪት መጎልበት ምንም ፋታ በማይሰጥ ፍጥነት ተዘጋጅቶ የትግሉ ባለቤት የሆነው ሕዝባችን ወሳኝ ጫናውን እንዲያሳርፍ እንዲደረግ ለአገራችን አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች፥ ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አንስቶ ለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ከአንጋፋው የመምኅራን ማኅበርና ከኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኅበር አንስቶ ለሌሎች የሲቪክ ማኅበራት መሪዎች፥ ለተማሪዎችና ለወጣቶች፥ ለሴቶች ማኅበራት፥ መሪዎችና ለሌሎች የሙያና ማኅበራዊ ስብስቦች አስቸኳይ ጥሪ እያስተላለፍን፤ አሁን ትግላችንና አገራችን ባሉበት አስጊና አጣዳፊ ሁኔታ ለትግል በተጠንቀቅ ከቆሙት በብዙ ሚሊዮን ከሚቆጠሩ ዜጎቻችን አንፃር ሲታይ በተለያዩና ከአቅም በላይ ሊሆኑ በሚችሉ ምክንያቶች አንዳንድ ኃይሎች ይኸንን የጋራ ጥሪ ለማስተላለፍ አለመቻላቸው እስከዚህም አሉታዊ ጫና ይኖረዋል ብለን ስለማናምን ይኸንን ጥሪ በጋራ ለማስተላለፍ የወሰኑት ወገኖች እንዲደባለቁንና በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትግሉን ህያውነት የሚያበስርና የሚያረጋግጡ ተከታታይ እርምጃዎችን ለመጠቆም እንድንችል አገራዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የግንቦት ድሎች በዜጎች የጋራ ተጋድሎ ይከበራሉ !

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ታኅሣስ ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም